# ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአተኞችን ይወዳል

**አዘጋጅ** ፡ የግብጽ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

**የመጽሐፉ ስም** ፡ ተከታታይ ጽሑፎች በመንፈሳዊ ሕይወት አጀማመር፡፡

## ክፍል ፩

## ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአተኞችን ይወድዳል

**አዘጋጅ** ፡የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

**ማሳሰቢያ** ይህንን መጽሐፍ ለመረዳት ያመቻችሁ ዘንድ ከመጀመሪያ ጀምሮ ያለውን እትም ብታነቡ መልም ነው ምክንያቱም ጽሑፎቹ ተከታታይ ናቸው፡፡

*ይህንን መጽሐፍ ሁሉም ኦርቶዶክሳዊ በቅናሽ ዋጋ እንደሚያገኝ ተስፋ አለን፡፡
*እናንተም ለወዳጆቻችሁ በማከፋፈል እንድትረዱን በእግዚአብሔር ስም እናሳስባለን፡፡

# መቅድም

ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአተኞችን ይወዳል የሚለውን ቃል ስሰማ ጣእም ያለውና በልብ ላይ ተስፋ የሚዘራ ሆኖ አገኘሁት፡ ፡ ምክንያቱም ሁላችንም ኃጢአያተኞች ነን። መጽሐፍ ቅዱስም በአንድነት የማይጠቅሙ ሆነዋል፤ ቸርነት የሚያደርግ የለም፡፡ ሲለን ሁላችንም እንደረከስን ነው የሚገልጽልን፡፡ ይሁን እንጂ ከነበደላችን በእግዚአብሔር የተወደድንና የተመረጥን ነን፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር እኛ ልጆቹን ፈውስ እንጂ ቅጣት እንደሚያስፈልጋቸው አድርጎ አያየንም።

ይህ ጽሑፍ የመንፈሳዊ ጉዞ መግቢያና መጀመሪያ ስለሆነ እግዚአብሔርን ማወቅ፣ እኛ ኃጢአተኞች ስለሆንን እኛ ላይ ያለው እይታ እና አግባብ አየያዙ እናያለን። የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ለመረዳትና ኃጢአተኞችን ተቀብሎ እንደሚቀይረን ለማወቅ እነዚህ ተከታታይ ጽሑፎች አብራቹን በማንበብ እንድትጨርሱት እንማጸናችኋለን። ይህ ተከታታይ ጽሑፍ ለእያንዳንዱ ሰው ቀለል ባለ አገባብና ውጤታማ በሆነ መልኩ የተዘጋጀ ነው።

ጌታ ዓይነ ልቡናችንን ይክፈትልን፣ ፍቅሩን እንድንቀበል ይርዳን፣ የእናታችን የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምና የቅዱሳን ሁሉ ጸሎት አይለየን፡፡ለአምላካችን ለዘለዓለም ክብር እና ምስጋና ይሁን፡፡ አሜን።

**ወደ** አባታችን የሔድኩት አንድ መንፈሳዊ ትምህርት መማር ከሚፈልግ ወንድሜ ጋር ነበር። እኔ ከአባታችን ብዙ ነገር ስለተማርኩ እርሱም እኔ የተማርኳቸውን ነገሮች እንዲማር እፈልጋለሁ። እኔ አባቴ ጋር መንፈሳዊ ነገር መማር ከጀመርኩ ጀምሮ ብዙ ነገር ተምሬአለሁ። አሁን ደግሞ እኔ የተማርኩትን እንዲማሩ እና እንዴት ከክርስቶስ ጋር ግንኙነት መጀመር እንዳለባቸው የማካፍልበት ጊዜው ደርሷል። እኔ በጀማሪ ደረጃ ስላለሁ ልረዳ የምችለው መማር የሚፈልጉትን ወደ አባቴ መጠው እንዲማሩ ማድረግ ነው እርሱ ከእነርሱ ጋር ይቀጥላል። እኔም ከእነርሱ ጋር መማር እንደምችል ነግሮኛል።

ጓደኛዬ ጥሩ ልብ ያለው እን እና ታማኝ ሰው ነው። ነገር ግን ባለፈው ሕይወቱ እና በአካባቢው ሰዎች ተጽእኖ ፈጽሞ ተቀየረ። ኃይለኛ እና ሱሰኛ እየሆነ መጣ። መንገዱ የኃጢአተኛ መንገድ ሆነ። ይሔ መፍረድ አይደለም ምክንያቱም እርሱ እና ጓደኞቹ የሚመሰክሩት እውነት ነው።በዚ የተነሳ ደግሞ ቤተክርስትያን መመላለስን እርግፍ አድርጎ ተወው።

የሚገርመኝ ነገር ግን ከሱ ጋር ቁጭ ብየ በማወራበት ጊዜ ገራገር ወደ ክርስቶስ ተመልሶ ረጋ ያለ ሕይወት መምራት የሚፈልግ ሰው ነው። እንዴት አድርጎ ይመለስ? ሰው ሁሉ በእርሱ ተስፋ ቆርጧል።ሁሉን ነገር አቁሞ በአንዴ መቀየር አልቻለም።።መጥፎ ልምድ ለማጠራቀም ብዙ አመት የወሰደበት በደቂቃዎች መቀየር አይችልም። ስንት ጌዜ ሞክሮ ነበር ግን አልተሳካለትም። አንዳንድ ጊዜ "ተስተካክየ አለው አዲስ ሰው ሁኘአለው" ሲል ይሰማና ከዛ ከትንሽ ጊዜ በኋላ ወደ ነበረበት ይመለሳል።ተስፋ ይቆርጣል ከራሱ ጋር ይጣላል ።

"ኡፍፍ. . . እኔስ እማይረባ ሰው ነኝ ለምንድን ነው ያልቀጠልኩት ይላል።አንዳንዴም እነዚህ የቤተ-ክርስትያን ሰዎች ግን መናፍቃን ናቸው ምንም ለውጥ የተባለ የላቸውም ቤተክርስትያን ውስጥ እንደ ጥሩ ሰዎች ያገለግላሉ ከቤተክርስትያን ግቢ ከወጡ በኋላ ግን በቃሎቻቸው አድርገው ለሰው እንቅፋት ይሆናሉ። ምን አይነት አታላይ ሰዎች ናቸው እያለ ተስፋ እሚያስቆርጥ ንግግር ይናገራል።

አንድ ቀን ግን ከራሱ ጋር ቃል ኪዳን ገብቶ መንፈሳዊ ጉባኤ ተሳተፈ እውነተኛ ንስሐ ሰውን ወደ

ኃጢአት አይመልሰውም የሚል ስብከት ሰማ፡ኃጢአትን በኃይል መታገል ጀመረ፡፡ በጀመረበት ሰዓት ግን በአንድ የተወሰነ ኃጢአት በተደጋጋሚ ወድቆ ተስፋ ቆረጠ“ **እውነተኛ ንስሐ ወደ ኃጢአት እማይመልስ ከሆነ ታድያ እኔ ንስሐ በመግባቴ ምን አገኘሁኝ**?! አለ። ቆይቶ ግን መንፈሳዊ ሕይወት የሚቀጥል ጉዞ እንጂ በአንዴ ብቻ እንዳልሆነ ከገባው በኋላ ከእንደገና አዲስ መንፈስ አገኘ፡፡ስለ አባታችን ከነገርኩት በኋላ በይበልጥ ብርታት በአዲስ መንፈስ ከአባታችን ጋር ተገናኘ፡፡ ያኔ እኔ ከወራት በፊት የጀመርኩት መንፈሳዊ ሕይወት እሱም ከኔ ጋር ሆኖ ለመቀጠል ወሰነ።

አንድላይ ወደ አባታችን እየድሔን ስለ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢአተኞችን ያለው ፍቅር እያወራን አባታችን ጋር ደረስን፡፡ አባታችንም ሲጠቡቁን ስለ ነበሩ ተቀበሉን፡፡ እኔም አባታችንን አስፈቀድኩኳቸው እና ብቻው እንድነጋገሩት ትቻቸው ወጣው ።

ጓደኛየ ከአባታችን ጋር ብቻየን ስለተወኝ በጣም ተሳቀቅኩኝ፡፡ ምክንያቱም ጸጉሬ ረጅም ነበር፡፡ አባቶች ረጅም የተጠቀለለ ጸጉር ብዙም አይደግፉትም ምን ላድርግ! ባህሪ እንደዚህ ከሆነ ስለእውነት ሁልጊዜ

ከራሴ ጋር “እግዚአብሔር ግን ረጅም ጸጉር አጭር ጸጉር ያስፈገዋል እያልኩ እመራመራለው። ብዙ ነገሮች ደፈር ብየ እንኳን ብፈታውም ስለእግዚአቤሔር እና ስለመንፈሳዊ ሕይወት ባሰብኩኝ ጊዜ ግን ትልቅ እፍረት ውስጥ እገባለዉ።

አባታችን ትሁትና ፈታቸው በደስታ የበራ ብቻ ሳይሆን ያለምንም ጥያቄና አስተያየት እኔን መቀበላቸው ለእኔ እርጋታ ሳይፈጥርልኝ አልቀረም። በሕይወቴ በጣም የምጠላው ነገር ቢኖር አንድ ሰው በግል ሕይወቴ ገብቶ ሲጠይቀኝ ነው። አብዛኞች ሰዎች “ለምንድን ነው ጸጉርህ እንደዚህ ያረዘምከው? ይሉኛል። እኔ ግን ደስ ስለማይለኝ በደረቁ “የእኔ ጸጉር ነው ወይስ ያንተ ጸጉር? ብየ ነው የምመልስላቸው። እኒህ አባት ግን እንደሊሎቹ አይደሉም ስለ ጽጉሬ ሳይጠይቁኝ “እንዴት አደርክ ልጄ” አሉኝ። ለረጂም አመታት የምንተዋወቅ መስሎ ተሰማኝ!

**እኔ**፡ እግዚአብሔር ይመስገን አባቴ

**አባታችን**፡ ሕይወትህ እንዴት ነው?

**እኔ**፡ ጓደኛየ እንዳሎት ነው ከአምላኬ በጣም እርቄአለው ብዙ ነገሮች ለመናገር የሚያሳፍርና የሚያደክም ነገሮች ሰርቻለው። ሁሉም አይነት

ኃጢያአት ሰርቻለው፡፡ ኃጢያአት አሸነፈኝ ብሎት ማጋነን አይሆንብኝም፡ሁሉም ትቼ ወደቀና መስመር ለመመለስ ስንት ጊዜ ሞክሬ ግን አቃተኝ።

እንዴት ብየ መንፈሳዊ ሕይወት እጀምራለው የሚል መጽሐፍ ካነበብኩኝ በኋላ ግን ትንሽ **ጥንካሬ ሰጥኝ** መንፈሳዊ ሕይወት ጉዞ እንጂ አንድ ምዕራፍ እንዳልሆነ ከተገነዘብኩኝ በኋላ ትንሽም ቢሆን ተስፋ አደርኩኝ። የሚገርሞት ነገር አባቴ ተስፋ በምቆርጥበት ሰዓት ወደ ፓጋን(አምላክ የለም ብሎ የሚያምኑ ሰዎች) እሔድ ነበር፡፡ እማድርገው ነገር ስለሚጨንቅኝ ራስህን አጥፋ ራስህን አጥፋ ይለኛል! እኔ እንጂ በቃ ውስጤ በጣም ተጎድቷል፡፡ ከነበርኩበት የጥፋት መንገድ የሚረዳኝና የሚያወጣኝ አለ ብየ ካስብኩኝ በኋላ ግን ወደ እርስሆ መጣው። በትልቁም እዚህ የተማረ ጓደኛየ በጣም ትልቅ ለውጥ በሕይወቱ ላይ ሳይ በጣም ተገረምኩት፡፡ ምክንያቱም ሰው ብሎት ሳይሆን የሚያስብልኝ ትክክለኛ ፍቅርና ከልቡ መልካምነት ነበር የሚያሳየኝ፡፡ ይኼ በጣም አስተማሪና ተግብራዊ የሆነ መጽሐፎትም ወደዚህ እንድመጣ በጣም ነው የረዳኝ።

**አባታችን**፡ ጥሩ አረክ ልጄ !! እሺ “እንደት ብየ ልጅምር” የሚል መጽሐፍ ማንበብ ከጀመርክበት ጊዜ

ጀምሮ ከለሳ ካደረጋችሁ በኋላ፡ ከእሱዋ ጋር ተያይዞ የሚሔድ ቀለል ያለች ርዕስ አለች እሱም

“**ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአተኞችን ይወዳል**” የሚል ነው። ስለዚህ ከመጀመራችን በፊት መሰረታዊ የሆነ ነገር እንድናይ ይገባናል።

**እኔ**፡ ርዕሱ ግን ደስ ሲል አባቴ እሱም ብቻ ሳይሆን ያበረታልም፡፡ በመንገድ ላይ እየመጣን እያለ ከጓደኛየ ጋር ስለርዕሱ ጉዳይ እንወያይ ነበር፤ እንዳየሁት ከሆነ ግን ከእርሶ ብዙ ነገር ነው የተማረው። ግን አባቴ ክርስቶስ ኃጢያአተኞችን እንደምያፈቅር ምን ማስረጃ አለ?!

ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢያአተኞችን እንደሚወድ ሶስት ጭብጥ ነገሮች እንመልከት

### የመጀመርያው ማስረጃየ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል ነው

**እኔ**፡ በሰፊው ቀስ ብለው ቢገልጽሉኝ ግን ጥሩ ነበር አባቴ ምክንያቱም የቤተክርስትያን ነገር ምንም እውቀት የለኝም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ቢሆንም አንብቤ አላውቅም፡

፡ ቅዳሴም ቢሆን በግዕዝ ስለሆነ ምንም አይግባኝም፤ ቻይነኛ መስሎ ነው ሚሰማኝ፡፡ ስለዚህ መንፈሳዊ የሆኑ ነገሮች ሲነግሩን አባቴ እንደ ህጻን ልጅም ምንም ነገር እንደማያውቅ አድርገው ቢያዩኝ ጥሩ ነው።

> የሚቻል ቢሆን በወጣትነት እድሜ ላይ እያለ ሁሉም ሰው በእግዚአብሔር ፊት የተከበረ እንደሆነ፤እግዚአብሔር የቀድሞው የሰው ልጅ ግርማ ለመመለስ ሲል በተከበረው በልጁ ደም እንደገዛው፤እንደውጤቱም ሰማያውያን ቅዱሳኖች እንደሚያፈቅሩት፤እግዚአብሔር በእኛ ላይ ያለው እይታ በፍቅር እንደሆነ፤ እንደዚህ ብለው ብያስተምርዋቸው እንዴት ምልካም ነበር።
> ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ (የአምላክ ፍቅር በሚል መጽሐፍ ላይ ገጽ 57)

**አባታችን፡** ህጻናቶችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያፈቅራቸዋል። ስለእነሱም እንደዚህ አለ እግዚአብሔር “መንግስተ ሰማያት ለልጆች እንደነዚህ ናት ልጅም ተውዋቸው ወደ እኔ እንዲመጡ አትከልክልዋቸው፡፡

(ሉቃ 18፡16) ኃጢአተኞችን እንደሚያፈቅር ወንጌላዊ ማርቆስ እንደዚህ ብሎ ተስፋ ሰጥው “ሕመምተኞች እንጂ ብርቱዎች ባለ መድኃኒት አያስፈልጋቸውም፤ ኃጢአተኞችን እንጂ ጻድቅን ልጠራ አልመጣሁኝም፡፡ (ማርቆስ 2፡17)

በተመሳሳይም ‹‹በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖሩ እንጂ እንዳይጠፉ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና›› (ዮሃ 3፡16)

እግዚአብሔር በኢሳ፡18 “ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ እሙዳይ ትነጻለች ፤ እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች” ይላል።

**እኔ**፡ ምን ማለት ነው ደምም? አባቴ

**አባታችን**፡ ደምም ማለት በጣም ደማቅ ቀለም ማለት ነው፡ እዚህ ምን ለማለት ፈልጎ ነው ሺህ ጊዜ እንደ ደም ብትቀሉም አትዘገኑኝም ወደእኔ ኑ እኔ አባታቹ እንደ በረዶና እንደ ሱፍ አነጻቸዋለው ይላል እግዚአብሔር።

**እኔ**፡ መልካም ዜና ነው፡፡ በዘመነ ኢሳያስ አንድም ሰው ጥሩ አልነበረም ማለት እኮ ነው !

**አባታችን**፡ ምንም ይሁን በደላችን እግዚአብሔር እንደ እሚያፈቅረንና እንደ ሚያስብልን ካላወቅን የአምላክ ቃል ካልገባን እንጠፋለን። ምክንያቱም እሱ የኃጢአተኞች ወዳጅ፤ ኃጢአታችንም እደሚጠርግልን ምህረቱ እንደሚያበዛልን ነው የተናገረው። (ኢሳ 55፡ 7). ሰይጣን ትልቁ አላማው ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግኑኝነት መበጠስ ነው። በአእምሮአችን እግዚአብሔር በኃጢአታችን ብዛት እንደሚስለችውና እንደማይመለሰን አድርጎ ያሳምነናል። እሱ ውሸታም ነው፡፡ የውሸት አባት ነው፡፡ (ዮሃ 8፡44)

**እኔ**፡ ታድያ እኔኮ ሁልጊዜ ነው ኃጢአት የምሰራው አባቴ ለዛም ትልቅ ኃጢአት የሰራሁት አለ!!

**አባታችን**፡ እኛ እማይገባን፣ ሕይዎታችን የሚያበላሽ፣ ከልሳናችን የማይለይ በተደጋጋሚ የምንላት ቃል አለች። ለእኛ ትህትና ይሚመስለን ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ግን የምያፈርስ ነው።

**እኔ**(በመገረም)፡ ምንድን ነው አባቴ ?

**አባታችን፡ “እግዚአብሔርን አስቆጣሁት”**

**እኔ**(በስሜት)፡ እንዴ ታድያ ተደጋጋሚ ኃጢአት ስሰራ እግዚአብሔርን አያስቆጣውም እንዴ?

**አባታችን**፡ በእነዚህ ኃጢአት መውደቅ ትወዳለህን?

**እኔ**፡ አረ አልወድም!! ከዛ ማነው የሚገላግለኝ?!! አልኩ

**አባታችን**፡ አዎ እንደዚህ ከሆነ እግዚአብሔርን አታስቆጣውም፡፡ እንድያውም አምላክ እንደዚህ ነው የሚልህ፡ “**ወዳጄ፡ ሰይጣን ነው እኔን እና አንተን ሊያቀያይመን የሚጥረው**”። ልክ አንድ በመንገድ ላይ እንደሚሔድ ህፃን ልጅ ነው፤ እየሔደ እያለ አንድ ተንኮለኛ ልጅ መጥቶ ቆሻሻ ዋሃ ልጁ ላይ ቢደፋለት አባቱ ለየተኛው ነው የሚቆጣው?

**እኔ**፡ እርግጠኛ ነኝ ውሃ ለደፋለት ልጅነው።

**አባታችን**፡ እኛም እንደሱ ነን፡፡ ኃጢአት ውስጥ ስንወድቅ እግዚአብሔር ተቀብሎን እንደ እሚያጸዳን አምነን ተሎብለን ወደ እሱ እንመለስ፤ እግዚአብሔርን አሳዝኘዋለው የሚል ቃል ሰይጣን ወደ ሰማያዊ አባታችን እንዳንመለስ፤ ከተመለስን መቅሰፍት እንጂ እርዳታ እንደሌለው አስመስሎ አእምሮአችን ላይ ያስርጽልናል። በዛም የተነሳ መቀጣት፣ ለመቀጣቱ እማ ዝም ብየ ኃጢአት ብሰራ ይሻለኛል ትላለህ፡፡ አንዳንዴም ተጠራጣሪ ልብ ይኖርሃል፡፡ ኃጢአቴን ይተውልኝ ይሆን ትላለህ፡፡ ከጊዜ በኋላ ተስፋ ስለምትቆርጥ ለመመለስ በጣም ይከብደሃል፡፡ በልብህ

ውስጥም “አምላክ በእኔ ተስፋ ቆርጧል በቃ ትላልህ”፡ ፡ በዚህ ሰዓት ዲያብሎስ **“እንኳን በእጇ ውስጥ ገባህ አሁን አለቅህም”**ይለሃል።

**እኔ፡** ይህን የሚያክል ተንኮለኛ አርድርጌ አስቤው አላውቅም!!

**አባታችን፡** ክርስቲያኖች ባሉበት አካባቢ ቤተ ክርስትያን አለመኖሩ አገልግሎት አለማግኘቱ ሰዎቹን ከወንጌል እንዲርቁና በአካባቢው በአል እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል። ከእውነተኛ የክርስቶስ ወንጌል የራቁ ይሆናሉ! ዲያብሎስም በቀላሉ ይጫወትባቸዋል። አንድ ሰውየ ሚስቱን ትቶ ወደ ጆርዳን የሚባል ሀገር ሔደ። ከሚስቱ ጋር ከተጋባ ሁለት አመት አድርጎ ነበር። አንድ ልጅም ነበራቸው፡፡ ከሔደ በኋላ በየወሩ ደብዳቤና ሕይወትዋን የምትቀይርበት ገንዘብ እንደሚልክላት ቃል ገብቶሏት ሔደ፡፡ ከመሔዱ በፊት ማንበብ ስለማትችል ለቤተሰቦቿ ወይም ለቤተሰቦቹ ሒዳ እንድያነቡላትና በየወሩም ብር አዘርዝረው እንደሚሰጥዋት ነግሯት ሔደ። ቃሉን ሳያጥፍ በየወሩ ብርዋንና ደብዳቤ ይልክላት ጀመር፡፡ እስዋም ቤተሰቦቿ ብር እንደመጣላት ሲነገርዋት ሔዳ ብር አዘርዝረው ሲሰጥዋት ተቀብላ ትመጣ ነበር፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ

የቤተሰቦቿ ቤት ሩቅ ስለነበር መመላለስ ሰልችተዋት ተወችው። አንድ መፍትሔ ብላ ያሰበችው ወደ ጎረቢትዋ ሒዳ ብር አዘርዝርልኝ ማለት ነበር። እርሱም ያዘረዝርላት ጀመር። ከወራቶች በኋላም የባልዋ ደብዳቤ አንብብልኝ ትለው ጀመረች። እሱም ያነብላት ነበር። ድጋሚም ከጊዜ በኋላ ፖስታ ቤት መሔድ ሰለቻት። ደብዳቤና ብር እንዲቀበልላት ደብዳቤ ለምያነብላት እና ለሚዘረዝርላት ጎረቤትዋ ውክልና ሰጠችው።እርሱም እንደልማዱ ተቀብሎ ያነብላትና ብር ያዘረዝርላት ነበር።

ከእለታት አንድ ቀን ልጅዋ ታመመ። ብዙም እውቀት ስላልነበራት ልጅዋን ችላ አለችው፤ እሱም በጣም ታመመ። ከሳምንት በኋላ ተሸሎት ወደ ነበረበት ተመለሰ ። እንደልማድዋ የባልዋን ደብዳቤ ለመቀበል መጣች። ጎረቤትዋም ይህን ችልተኛነቷን አይቶ፤ የልጅዋም መታመሙ ተጠቅሞ ደብዳቤው ባልዋ ልጁ መታመሙን እንዳወቀ አድርጎ ነገራት። ልጁን የታመመው እሷ ስለማትንከባከበው አሁንም ትዳራቸው በጥያቂ ምልክት እንዳለ አድርጎ አነበበላት። ሴትየዋም ስለአመነችው በጣም ፈራች። እሱም መፍራትዋ ካወቀ በኋላ ሴራ ጠነሰሰ። «አይዞሽ አትፍሪ እኔ አለውልሽ»

እያለ ሊጠቀምባት ፈለገ። በተመሳሳይ ባለቤቷ እደጻፈላት አድርጎ ራሱን የጻፈው ውሸት ያነብላት ጀመር። አጠግብ ለአጠገቡም የፍቅር ወሬ ያወራታል። ከክርስቶስና ከቤተ ክርስትያን ስለ ተለየች። ከፍራቻ የተነሳ ከጎረቤትዋ ጋር ተጋባች። ከሁለት አመት በኋላ ትክክለኛው ባለቤቷ ወደ ሀገሩ ከተመለሰ በኃላ አስፓልት ላይ ፊት ለፊት ተገናኙ። በጣም ጮክ ብላ "ከአሁን በኋላ ከእኔ ጋር ምንም ነገር የለህም፤ የሆነ ነገር ማድረግ ካሰብክ ፖሊስ ጋር እደውላለው" ብላ አስፈራችው። እሱ በበኩሉ በድንጋጤ "ምንድነው እያልሽ ያለሽው?"አላት እሷም ግን "አንተ ባለቤቴ አይደለህም አላውቅህም" ብላው ሔደች። ከብዙ ጊዜ በኃላ ግን ሁሉም ነገር እውነቱን ካወቀች በኋላ በጣም አዘነች ምን ታድርግ ታድያ።

**አንተም** መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተጽፎ እንዳለቃል ፍቅርና ተስፋም፤ ከመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካልተቀበልክ እጣህ እንደ ሴትየዋ ነው የሚሆነው። እግዚአብሔር አምላክ እንዳስቆጣኸው ባንተ እንደሰለቸውና እንደሚቀዝፍህ፤አንዴ የመዳን እድልክ እንዳለፈብህ፤ ሁለተኛ በኃጢአት ብትወድቅም እንደማይምርህ የሚል መጥፎ ሃሳቦች ጭንቅላትህ ላይ

ታስቀምጣለህ። ይኼኔ አቅጣጫህ ስተሃል ማለት ነው። ለእኛ ቀንደኛ ተስፋ የሚይያስቆርጠን ይህ ነው። ከእግዚአብሔር ያለን ግንኙነት ያበላሽብናል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉንም ኃጢአተኞ ይወደል፤ አመንዛሪ አታላይ ነህ የት ነበርክ አይልም መመለሳችንን እይቶ በፍቅር ይቀበለናል እንጂ።እንደዚሁ ያለ ምንም ምክንያትና ሁኔታ ሰውን የሚያፈቅር ጌታ ማንንም ሳይለይ ሁሉንም ለማዳን በመስቀል ላይ ሞተ፤ምህረት ሰጠ።

**እኔ**፡ ቆይ አንዴ እዚህ ላይ አባታችን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እዚህ አለም ላይ እያለን ያለ ምንም ልዩነት ነበር ያፈቀረንና ያዳነን ?

**አባታችን**፡ እግዚአብሔር ንስሐ ሳንገባ እያለን ከነኃጢአታችን ነበር የወደደን። ንስሐ ግቡና ከዛ እወዳችዋለሁ አላለም። ለእያንዳንዱ ሰው በሕይወቱ ላይ “**አንድ አስፈላጊ ነገር**” መጽሐፍ ቅዱስ ላይ አለ። እሱንም ያመነ ሕይወት ከሽንፈት ወደ ማሸነፍ፤ ከዲያብሎስ ግዛት ወደ ክርስቶስ ነጻነት፤ ከጨላማ ኃጢአት ወደ ጽድቅ ብርሃን ይመጣል።

**እኔ**፡ ምን ላይ ይሁን የኼ ጥቅስ አባታችን?

**አባታችን፡** የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ 5፡8 **“እኛ ገና ኃጢአተኞች እያለን”** እለን ገና ኃጢአተኞች እያለን ንስሐ ሳንገባ ሳንቀየር ሳንመለስ ማለቱ ነው።

> የምህረት አባት የሚወደውን ልጁን በድካሙና በስራው አይጠላውም፤ ምንም ያህል መጥፎ ቢሆንም፡፡ ከድካሙና ከኃጢአቱ ሊያድነው እና ፍቅሩን ሊገልጽለት እጆቹን ወደእርሱ ይዘለጋል፡፡እግዚአብሔር የሚደነቅ የነብስ ሐኪም ነው፤ ምንም ያህል የከፋ በሽታ ላይ ቢወድቁ እናኳን በሽተኛውን ይወደዋል፤ ነገር ግን ፍቅሩ ለበሽተኞች እንጂ ለሽታው አይደለም።
> (መምህር ኦሪጋኖስ፡ የአምላክ ፍቅር ገጽ 365)

“ክርስቶስ ኃጢአተኞች ሳለን ስለእኛ ሞተ፤ ፍቅሩን በመስቀል ላይ ገለጸልን።”

ይህ ማለት ልጁ እግዚአብሔር ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ወይም ያለማዳላት ፍቅሩ ገለጸልን። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በኃጢአት ውስጥ እያለንም እንደሚወደንና እንደሚቀበለን ካላመንን እውነተኛ ንስሐ ለመግባት ይከብደናል።

**እኔ፡** እንዴት ማለት ነው?

**አባታችን**፡ ብቻችን ልንወጣው ስለማይቻለን፤ ክርስቶስ ኃጢአተኞችን ልያነጻን መጣ፡ እሱ ሐኪም ሆኖ ልያድነን እኛም መዳን የፈለግን በሽተኞች ነን።

(እንደ ድንገት አባታችን ሆዳቸው ይዘው አአአ... እያሉ ያቃስቱ ጀመር)

**እኔ**፡ ምነው አባታችን ምን ሆኑ?

**እኔ**፡ ህክምና እንሒድ? ደህና ነዎት?

**አባታችን**፡ ደና ሲሻለኝ፡ እንሔዳለን፡፡ አአአ..

**እኔ**፡ እንሒድ እንጂ አሁን? እንደዚህ ካልኩዋችው በኋላ ሳቁ ከተሻለኝ እንሒድ እንጂ(ገብቶሃል ያልኩት)አሉኝ?

**እኔ**፡(ፈገግ አያልኩኝ) አስደነገጡኝ እኮ፡፡ ልያስተላልፉት የፈለጉት መልእክት ግን በቀላሉ ገብቶኛል፡፡ (እንደዚህ ከማድረጎት በፊት ግን እንዳልደነግጥ ቢነግሩኝ መልካም ነበር )

**አባታችን** ፡ መጀመርያ ይሻለኝና ከዛ ህክምና እሔዳለው የሚባል ነገር የለም! ምክንያቱም እንዲሻለኝ ነው ወደ ህክምና የሚሔደው። ስለዚህ መጀመርያ ከኃጢአቴን ልንጻ ከዛም ወደ ክርስቶስ ሒጄ ፍቅሩ ልቀበል የሚባል አነጋገር ትክክል አይደለም፤ እንድናምነውም አይገባንም።

**እኔ፡** በጣም አጸያፊ በሆነ ኃጢአት ስወድቅ እግዚአብሔር ያወደኛል ማለት ነው?

> ኃጥአት በበዛበት ጸጋ ይበዛል።
> (ሰርዓተ ቅዳሴ)

**አባታችን፡** አዎ!! ኃጢአትህ በሚበዛበትም እግዚአብሐየር በጣም ይወድሃል፡፡ ሮሜ 5፡20 ላይ አንደተጻፈ «ኃጢአት በሞት እንደነገሰ፤ እንዲሁም ጸጋ ከመጠን ይልቅ በለጠ።

**እኔ፡** ምንም አልገባኝም ለመጀመሪያ ግዜ ነው የሰማሁት ጥቅሱ ?

> ኃጢአት በሞት እንደነገሰ፤
> እንዲሁም ጸጋ ከመጠን ይልቅ በለጠ።
> ሮሜ 5፡20

**አባታችን፡** አንድ የአጥንት ሐኪም አምስት ልጆች ነበሩት ከእነሱም አንዱ ኳስ እየተጫወተ እያለ እግሩ ይሰበርና ወደ ህክምና ወስዶ ጆሶ አስጠቀለለለት፡፡ ከልጆቹ የተኛው ነው እንክብካቤ የሚስያስፈልገው?!

**እኔ፡** ይኼማ የታወቀ እኮ ነው ለተሰበረው ልጁ ነዋ!

**አባታችን፡** ከተወሰነ ቀን በኋላም ሌላኛው ልጁ ከደረጃ እየወረደ እያለ ወድቆ ወገቡን ተመታ፡፡ አሁንስ ማንን አብልጦ ይከባከብ?

> በኃጢአት ስትወድቅ እንዴት እኔን ውድቀት ያጋጥመኛል ብለህ አትመካ፣ ይኼ የትዕቢት አዋጅ ነው። ማንነትህን ዝቅ አድርገህ፣ አይንህን ወደ ሰማይ አድርገህ ከልብህ እኔ ደካማ ኃጢአተኛ ነኝ ስንፍናየን አስወግድልኝ፡፡ ልክ በሌለው ምህረትህ ባትረዳኝ ወደ የከፋ ኃጢአት እወድቅ ነበር፡፡ አሁን ግን አመሰግናሃለው።ብለህ አመስግነው።
> (ቅ/ቲዮፊን አልናስክ 2ኛ)
> (ክፍል ገጽ፡86)

**እኔ፡** አሁን ወገቡን የተሰበረው ነው የሚንከባከበው ?

**አባታችን፡** ከሳምንት በኋላም በመኪና አደጋ ትንሹን ልጁ ሰርሰሩን ተሰበረ አሁንስ ለማናቸው አስበልጦ ነው የሚንከባከበው ትላለህ፣ ለእዛ ላልተሰበረው ወይስ እግሩን ለተሰበረው ነው ወይስ በመጨረሻ አደጋ ላጋጠመው?

**እኔ፡** ለመጨረሻው ለተጎዳው እንጂ ምክንያቱ የእሱ ሁኔታ ከባድ ነው ።

**አባታችን**፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እንደዚህ ኃጢአተኞች ያፈቅራቸውም ያስብላቸዋልም ። ሌላ ምሳሌም እንውሰድ ለአንድ የጠፋች በግ ዘጠና ዘጠኝ በጎች ትቶ አንድዋን ሊፈልግ መጣ ምክንያቱም በጣም አንክብካቤ የምያስፈልጋት ያቺ መጥፎ ሁኔታ ስላለች ነው። ሰይጣን ውሸታምና የውሸት አባት ነው።

> እግዚአብሔር ኃጢአትን ፈጸሞ ይጸየፋል ነገር ግን ኃጢአተኛ ልጆቹን አይጠላም።
> ቅዱስ ዮሐንስ

(ዮሐ 8፡44) ግን “ጌታ ባንተ ሰልችቶታል፤ እግዚአብሔር አምላክ የሚወደው ቅዱሳንን ነው አንተ ግን ገሃንም ነው ቦታህ” ይለናል።

ያለኢየሱስ ክርስቶስ ነብሱን ራሱ ልያድንና ከኃጢአት ነጻ ለመሆን የሚፈትን መውደቁ የማይተርፍ ነው። የዚህ ውጤትም እግዚአብሔር ወደ ገሃነም ነው ሚወረውረኝ፤ ብሎ ስለሚፈራ የአምላክ ቃል ወደ ጥላቻና ወደ አለመቀበል ደረጃ ያደርሳል። ሰንበት ትምህርት ቤት ይማር የነበር የስድስት አመት ልጅ ነበር። ሁልጊዜ በትምህርት ማሃል ይጫወትና ይረብሽ ነበር። በጣም ስላበዛው አስተማሪው አንዴ ላስፈራራው

ብሎ በአምላክ ቤት የሚጫውት ልጅ አምላክ ወደ እሳት ይወረውረዋል ብሎ አስጠነቀቀው። ከዛ ልጁ ወደ ቤቱ ከተመለሰ በኋላ ወደ ማዕድ ቤት ገብቶ የኢየሱስ ክርስቶስ ሰዕል ይዞ በእሳት አቃጠለው። እናቱ ካየችው በኋላ በድንጋጤ እየሮጠች መጥታ "አንተ ልጅ ምን እያደረክ ነው?" አለችው፡ ልጁም "እሱ ቀድሞ ወደ አሳት ሳይጥለኝ እኔ ቀድሜ ላቃጥለው ብየ ነው" ብሎ በፍርሃት መለሰላት፡፡ አናቱም እንዴ ምንድነው ምትለው እንተ ልጅ ብላ ደግማ ጠየቀችው፡፡ ልጁም ቤተ ክርስትያን ሔጄ እያለው አምላክ ወደ አሳት ይከተሃል አሉኝ። እኔም ሳያቃጥለኝ በፊት ቀድሚ አቃጠልኩት ብሎ መለሰላት።

**እኔ፡** ይኼን ያህል !!

**አባታችን፡** አዎ ልጄ ! መጽሐፍ ቅዱስ እንዳለው ክርስቶስ ከኃጢአታችን ጋር እያለን እንደሚወደንና እንደሚቀበለን ካላመንን ጌታን መቀበል ይከብደናል፡፡ ከዛም አልፎ ያለምንም ማገናዘብ አምላክን ወደ መጥላት ደረጃ እንደርሳለን፡፡ ቅዱስ አጎስጢኖስ እንደዚህ አለ፡ "አምላክ የለም ብሎ የምያምን ሰው፤ አምላክ የለም የሚል ምክንያት ማግኘት ያስቻለው ምኞቱ ነው (ገንዘብ፡ዝና ፡ጾታዊ ስሜት...)"

አምላክነን የማይቀበል ስው በኃጢአቱ በምኞቱ ምክንያት አምላክ ይጠላኛል ብሎ ነው የሚያምነው። ከኃጢአቱ እያለ እግዚአብሔር እንደሚወደውና እንደሚቀበለው ቢያምን ግን ያንን ለውጥ እዚህ ላይ ነው የሚጀምረው።

**እኔ**፡ እግዚአብሔር ስለእሚያፍቅረኝና ስለሚቀበለኝ ኃጢአት ማድረግ ችግር የለውም ማለት ነው አነጋገሩዎት?

**አባታችን**፡ ያ ልጆችሁ በአደጋ የተሰበሩበት አባት ሁሉንም ልጆቹ ይወዳቸዋል፤

> እግዚአብሔን ባለማወቅ ለሚመጣ የነፍስ ሞትን እንጅ ሞትን እራሱን ልንፈራው አይገባም፤ሞት በእግዚአብሔርን ለማያምኑት ነው።።
> (ቅዱስ አንቶኒዋስ)

እንዲሰበሩና እንዲታመሙ ግን ፍላጎቱ አልነበረም። ስለዚህ አምላክም ከነኃጢአታችን ይወደናልም ይቀበለናልም። ኃጢአት እንዲኖረን ግን ፍላጎቱ አይደለም።

**እዚህ አለም ያሉ ሃብታሞች ግብዞች አንዳይሆኑ፤ ብዙ እዳይደሰቱ፤ይኼን**

**ሁሉ በየዋህነት በሰጠን በአምላክ እንጂ በዚህ በሚያልፈው ሃብት አንዳያምኑ አመኑ።። (1ኛ ጢሞ፡6፡ 7)**

ኃጢአት ማለት ልክ በአስፓልት ላይ እየሔድክ ሌቦች ራስ ራስህን ሲጨፈጭፉህ ነው። ሰማያዊ አባትህ ደሞ አይዞህ ወዳጄ ልንከባከብህና እዋጋልሕሃለው ብሎ ያረጋጋሃል።። እንድ ሰው ግን ሰማያዊ አባቴ ስለሚዋጋልኝና ስለሚያረጋጋኝ ዲያብሎስ መጥተህ ምታኝ የሚል ቢሆን ምን ትመክረው ነበር ?

**እኔ፡** ይኼማ እብደት ነው! ይቅር አይበሉኝና ?

**አባታችን፡** ዲያብሎስ ሲጥለን እግዚአብሔር አምላካችን ግን ያስነሳናል። ከኃጢአት ድካም፣ጉዳት፣ ራስህን መውቅስ፣ፍርሃትንና ከማነኛውም ድንጋጤ ፡ ለመንከባከብ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስፈልገናል። አንድ ጤናማ ሰው አምላክ እንድያዝንልኝ ሒጂ በሰይጣን ተመትቼ እመጣለው ማለት የለበትም።

**እኔ፡** መልካም አባታችን አንድ ትልቅ ነገር አስተምሮውኛል።። ቀደም አድርገው ግን የእግዚአብሔር ፍቅርና ምህረት አያዳላም ብለውኝ ነበር፣ እኔም ንስሐ ልግባ አልግባ ያለምንም እግዚአብሔር እንደሚወደኝ ብቻ አድርጌ ወስጄው ነበር።። እግዚአብሔር

ስለምያፈቅረኝም ወደ እርሱ እንድመለስ ረድቶኛል ማለት እችላለው፡፡ ግን ንስሐ ሳንገባ ነው ምህረት ያገኘነው ስንል አንዴት ማለት ነው? ንስሐ ሳንገባ ኃጢአታችን ሊተውልን ይችላል ማለት ነው ?

**አባታችን፡ ተቆጨን ማለት ምህረት አገኘን ማለት አይደለም፤ እሱ የምህረት መንገድ ነው።**

**እኔ፡** ይቅርታ አድርጉልኝ አባቴ አልገባኝም፡፡

**አባታችን፡** ያ የጠፋ ልጅ የአባቱን ብር ይዞ ከሔደ በኋላ ከአመንዛሪዎች ጋርና ከመጥፎ ሰዎች ጋር ሆኖ ብሩን አጠፋው፡፡ ከዛም መጠግያ አጥቶ ከአሳማ ጋር መተኛት ጀመረ። አባቱ ግን ያፈቅረው ስለነበር ቢ እያየ ይ ጋር አየኖረ፤ አባቱ ግን ልቡን በፍቅር ሞልቶ ስለነበር ይቅር ይለውና ሁሉም ነገር ይተውለት ነበረ። ቁጭት (ንስሐ) ለጠፋ ልጅ ፡ የአምልክ ምህረት እንዲያገኝ የሚረዳው መንገድ ነው።

ስለዚህ ቁጭት የምህረት መንገድ ነው

ምህረት ግን ከመመለሱ በፊት ነው የነበረው፡ ወደ ምህረት ካላመራ ግን ምህረቱን እያለ ሊያገኘው

አይችልም። ኢሳ፡44፡22 ላይ «እኔ ነኝ እምዋጅህና፤ ወደ አኔ ተመለስ» የሚል ስናይ፣**ገና ከመመለስክ በፊት እዋጀሃለው አላለንም**፡፡ መጀመርያ ተመለስ ከዛ በኋላ ግን እዋጀሃለው አለን። ስለዚህ ከተመለስኩኝ በኋላ ነው ምህረቱን የማገኘው።

**እኔ**፡ እግዚአብሔር እንደማረኝ አውቄአለው፣ ተጸጸትኩኝ ማለት ምህረት አገኘሁኝ ማለት አይደለም፡ ፡ ወደ ምህረት ሳመራ ነው የእግዚአብሔርን ምህረት የማገኘው፤ ባይሆን ግን ምህረት ቦታው ላይ ሳለው ባለመመለሴ (ንስሐ ባለመግባቴ) እንደምጠፋ አሁን ገብቶኛል አባቴ !

አሁንም የሆነ ዝብርቅርቅ የሚለኝ ነገር አለ፡፡ እግዚአብሔር አምላክ የሰው ጥፋት አይፈልግም ሰው ልጅ ግን የሚርቀው በራሱ ፍቃድ ነው፡፡ ሞትም ያመጣል እንላለን፡ ግን እኔ ይኼ ከጌታ ጋር እያራቀኝ ያለው ገዢ ፍላጎቴ እንዴት ብየ ከእኔ አርቀዋለው፤ ምክንያቱም

> መተላለፍህን እንደ ደመና ፣ ኃጢአትህንም እንደ ጭጋግ ደምስሼአለሁ፣ ተቤዥቼሃለሁና ወደ እኔ ተመለስ።
> (ኢሳያስ 44፡22)

ፍላጎቶቹ ሁሉ ክፋትና ርክሰት የተሞላባቸው ናቸው።

**እኔ በእግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ በፍላጎቶቹ መገዛት አልፈልግም፡በኃይልም ቢሆን እሱ አንዲመራኝ እፈልጋለው!!**

**አባታችን**፡ ይኼ ነው እውነተኛ ቁጭት ልጄ!!

እውተተኛ መንፈሳዊ ሕይወት የሚባለው በእንደዚህ መልክ ነው የሚጀምረው፡፡ በዚህ አጋጣሚ ትልቁና ከባዱን ደረጃ የሚባለው ተሻግረኸዋል። በተጨማሪ እውነተኛ ቁጭት የሚባለው ኃጢአትህን አምነህ ሕይወትህን ሊመራው ለሚችለው ጌታ ሙሉ ፍቃድ መስጠት እንጂ ምክንያት አምጥተህ ነብስህን ማጽናናት አይደለም። የእግዚአብሔር ቃል የታመነ ነው “ያ ወደኔ ሚመጣው ከቶ ወደውጭ አልጥለውም” ይለናል (ወንጌላዊው ዮሃንስ 6፡37) ሕይወትህ ሊመራ ፍቃድህ እስከሰጠኸው ድረስ እሱ ራሱ ያስጠጋሃል፡፡ «ሳትሰናከሉ እንዲጠብቃቹ በህብረትም ፊት በደስታ ነውር የሌላቹ አድርጎ በክብር ሊያቆማቹ ይቻለዋል» (የይሁዳ 1፡24)።

**እኔ**፡ ከአሁን በኋላ ኃጢአት ላይ በድጋሜ አልወድቅም ማለት ነው አባቴ?

**አባታችን**፡(ፈገግታ) እንደዛ ማለቴ አይደለም፡፡ ከታመምክ በኋላ ነብስህ ወደ ወዳጂህ አምላክ አስረክባት፡፡ እሱ ፍቱን ሐኪም ስለሆነ ኃላፊነት ስጠው፡፡ እንዴት አድርገን መዳን እንዳለብን እርሱን ነው የሚመለከተው፡በአንድ ላይ አይደለም እምንድነው፣ ጊዜ ልንስጠው ይገባል።

**ህክምናውን (ጸጋ የሚሰጥ ተግባር) መቀጠል አለብህ ፣ሐኪሙ የሚሰጥህ መምርያ(ወንጌል ማንበብ)ስትከተል ነብስህን ከምያሳምሙ ምግቦች (የሰይጣናዊ ስራዎችህ) ትቆብጥባለህ፡፡ ከጊዜ በኋላ እየአስተካከልክ ትሔዳለህ።**

ትልቁ የምያግዝህ ነገር ግን በሐኪምህ መተማመን አለብህ መንፈሳዊ አባትህን ማለት ነው።

**1ኛ በፍቅሩ ማመን** ፡ ፈገግታና ጣፋጭ ቃላት፡ የሐኪም ስራ በሽተኛ ለማዳን ትልቅ ሚና አለው፡፡ እንደማይጎዳህ ባንተ ላይ ፍቅር እንዳለው ካመንክ ፡ ለምንድነው የምትታመመው ለአንተ ህክምና አይገባህም ብሎ እንደማያባርርህ ታውቃለህ።

**2ኛ፡ በችሎታው መታመን**፡ እንዲሁም ሐኪምህ (እግዚአብሔር) ከሁሉም ህመመህንና ስቃይህ

እንደሚፈውስህ፤ ከሁሉም ኃጢአትህ ነጻ እንደሚያውጣህ በራስ ተማማኝነት ማመን አለብህ።

**እኔ**፡ በእውነት ግን ከሁሉም ሱሴንና ኃጢአቴ ነጻ ልያወጣኝ ይችላል?

**አባታችን**፡ መጽሐፍ ቅዱሳችን “በዚያን ቀን እንዲህ ይሆናል ይላል፡ እግዚአብሔር ከኃዘንና ከመከራ ከተገዛህለትም ከጽኑ ባርነት ያሳርፈሃል» (ኢሳ 14፡3) ይለናል።

## አምላክ በርግጥ ይሆናል ብሎዋል።

**እኔ**፡ በእውነት በምድር ላይ ይኼን የምናይበት ቀን አለ፤ ማለት ያለሱስ፣ውድቀት፣ ርክሰት ምንኖርበት ቀን አለ?

**አባታችን**፡ እንደዛ ማለታችን አይደለም፡ አላማውም እንደዛሜ አይደለም

**አላማችን ከእግዚአብሔር የእውነት ፍቅር የተሞላበት ወዳጃነት መፍጠር ነው።** ያ ልጅ ተሸሎት፣ ተነስቶ ኳስ መጫወት፣ከአባቱ ጋር መሳቅ ይጀምራል። በሕይወት እስካለ ድረስ ግን ሊጎዳ ባህርያዊ ነው። ከአባቱ ጋር ስላለ ተረጋግቶዋል፤ ሌላ ነገር ብያጋጥመው እንኳን አይተወውም። ልጁን የመንከባከብ ዋስትና

ሙሉ ኃላፊነት የሚወስደው አባቱ ነው፡፡ (ወደ ዕብራውያን 7፡22)

**እኔ**፡ በእውነት ቃሎት ምግብ ሆነኛል አባቴ፡ “አንተ ኃጢአተኛ አንተ በጌታ ፊት እምትረባ ሰው አይደለህም፤ አንተ ቆሻሻ ነህ” እያለ ሰይጣን ሃሳቤን ሲረብሸኝ በመቆየቱ እኔ ባደረግኩት ክፉ ተግባር ጌታ እሚቀበለኝ መስሎ አይሰማኝም ነበር። አሁን ግን ብርታት አግኝቻለው። ወጣት እያለሁኝ አፍላ እድሜ ላይ ወደ ሱሱና ሌላ መጥፎ ነገሮች መግባት ጀመርኩኝ፣ አጸያፊ ነገሮች መከታተል ጀመርኩኝ ይገቦውታል ብየ ተስፋ አደርጋለው አባቴ?

**አባታችን**፡ ገብቶኛል ልጄ አንተ ላይ ብቻ አይደለም፤ በዚህ እድሜ ላይ ያሉ ሁሉም ወጣቶች በእንደዚሁ አይነት ኃጢአት ነው እየተሰቃዩ ያሉት።

**እኔ**(ውስጢ ደስታ እየተሰማኝ)፡ በእውነት አባቴ?!

**አባታችን**፡ ብዝዎች ወጣቶች በሱስና ዝሙት ከወደቁ በኋላ፤ሰይጣን ለነብሳቸው የተፈነፈኑ ቆሻሻዎች እንደሆኑ ለማሳመን ይታገላቸዋል። ተስፋ ስለምያስቆርጣቸው እግዚአብሔር እንደሚምራቸው እያምኑም፡፡ በቃ አለቀልኝ ሰይጣን አሸንፎኛል ይላሉ፡፡ እውነቱን ግን እንደዛ አይደለም።

**እኔ**፡ (የልቤን ስለተናገሩ ቸኩየ)፡ እንዴት ማለት ነው?

**አባታችን**፡ አንድ ሐኪም የበሽተኛውን ፋሻ ሲቅይርለት በመረጋጋትና በፍቅርን ነው የሚቀይርለት፡ ፡ የሰይጣን ፈተና ለካ ጊዚያዊ ትግል ነው። ትንሾች አያለን፣ ከአስፓልት በለመድነው ስድብ ውሸት መሃላ አድርጎ ይጣላናል፡፡ ወጣቶች እያለን በዝሙት፣ሱስ አድርጎ ይጣላናል፡፡ከትምህርት ቤት በኋላ ስንመረቅ ወደ ስራ መግባታችን ደሞ በኃላፍነትና አስተሳሰብን አድርጎ ይጣላናል። ከትንንሾች ጋር የሚያንስ፤ ከትልልቆችም አብሮዋችው የሚያረጅ፤የወጣቶች ሰይጣን ግን በጣም ጠንካራና ኃይለኛ ነው። በባህርያቸው ወጣቶች ኃይልና ጤናማነት ስለሚሰማቸው ወደ ኃጢአት ሲወድቁ በጣም ይረበሻሉ፡፡ ከኃጢአት መታገል የችሎታ ጉዳይ አድርጎ ስለሚወስዱት እንዴት ብየ እኔ ኃጢአተኛ እሆናለው ይላሉ ለምሳሌ፡ አንድ ወጣት በእግር ካስ ጨዋታ ስናየው ሲሸነፍ በጣም ይረበሻል በጣምም ይሰመዋል።

**እኔ**፡ በእርግጥ እኔም የኮምፒተር ጌም ጨዋታ ስሸነፍ በጥም ይሰማኛል፡፡ ከዛም አልፎ ኮምፒተሩ ስበረው ስበረው ይለኛል።

**አባታችን**፡ በመንፈሳዊ ሕይወታችንም ለዲያብሎስ ብለን አንጣላለን፡፡ስለዚህ ከወደክ ተስፋ ሳትቆርጥ ተነሳ፡፡ “አንተ እማትረባ ሰው አይደለህም” የሚለውን ድምጽ አትስማው።

**እኔ**፡ እንደዚህ እያለ ከተጣላኝ ምን ማድረግ አለብኝ አባታችን?

**አባታችን**፡ “**የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከሁሉም ኃጢአት አንጽቶኛል**” ብለህ መልስለት። ክርስቶስ የሚል ስም አንደ ሰይፍ ተጠቅመህ ጣለው፡፡ እሱ ቀድሞ ሳይጥልህ፡፡ በእግዚአብሔር ፊት የተቀበልክና የተወደድክ እንደሆንክ፡፡ በደም ኢየሱስ ክርስቶስ እንደነጻህ እመን፡፡ለምን በቀን ሚልዮንን ጊዜ ብትወድቅም፡ሳትጠራጠርና ተስፋ ሳትቆርጥ ብቻ ተመለስ።

**እኔ**፡ በእርግጥ ይኼ የሰይጣን ምክር ጆሬየ ላይ መጥቶ ተስፋ የመቁርጥ ብቻ ሳይሆን እስከ ማበድ ነው የሚያደርሰን። አባኮዎትን አባቴ ፤ ለአንድ ጓደኛየ መንፈሳዊ ትምህርት(ካሪክለም) እንደጨረሱለት ለእኔም ከአጠገቤ ይሁኑ (አበረታቱኝ)፡፡

**አባታችን**፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አይተወንም። አንድ በአንድ እንዴት አድርገን ከተደጋጋሚ ውድቀት እንድናለን፤ እንዴት ብለን ኃጢአታችን እንደተወልን እናምናለን፤ሚለውን እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ እንወያያለን፡፡በእርግጥ ብዝዎች **ወጣቶች ራሳቸውን ከመውቀስ የተነሳ፡ በስነ አእምራዊ ጭንቀት ይኖራሉ** ።

**እኔ**፡ በተግባር መለማመድ እፈልጋለው አባቴ ! ጓደኛየ በሕይወቴ ውስጥ የተማርኩት ሁሉ በተግባር እያዋልኩኝ እንዲሔድ ይመክረኛል።የሚሰጡኝ ተግባር

ላይ የሚውል ስራ ከአቅሜን ጋር የሚሔድ ቢሆን ጥሩ ነው ምክንያቱም ሕይወቴን እንደምታዩት ነው ።

**አባታችን**፡ ውጤት እንድናገኝበት ተግባራዊ ስራ ስለሆነ በተግባር እናውለዋለን። አጀማመራችን በሁለት ደረጃዎች ነው ምንጅምረው፡፡ አንደኛው አስተሳሰባችን፣ በህብረተሰቡ ምክንያት ይዘነው የነበረው ሃሳባችን መቀየር ነው። ሁለተኛው ግብራችን ነው፡፡ይኼ ግብራችን እያልን ያለነው በተግባር ስንተገብረው ነው። አስተሳሰባችን እንድንቀይር እሚረዳን ሦስት ቀለል ያሉ አገባብ አሉ።

**እኔ**፡ ምንና ምን ናቸው

**አባታችን**፡ አንደኛው ወንጌል ማንበብ

**እኔ**፡ ከተወለድኩኝ ጀምሮ እንዴ ወይም ሁለቴ እንኳን አንብቤ አላውቅም!!

**አባትችን**፡ ግድ የለህም አንብበህ እማታውቅ ከሆንክ በቀን አንድ ጥቅስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ ጀምር ።

**እኔ**፡ አንድ ብቻ!!

**አባታችን**፡ አደራ ልጄ እኔ ያልኩህ አድርግ፤ በቀን አንድ ጥቅስ

> ሐኪሞች ሕመምን እንደሚጠሉና በሽታውን ለማስወገድና ታካሚውን ለማዳን እንደሚሰሩ ሁሉ እግዚአብሔርም በኃይሉና በክበሩ ኃጢአታችንን ሊያጠፋና ነጻ ሰው ሊያደርግን በእኛ ላይ ይሰራል፡፡
>
> (ቅዱስ አውግስጢን)

ለሳምንት ፤ በቀን ሁለት ጥቅስ ለሁለተኛው ሳምንት፤ በሦስተኛው ሳምንት ደግሞ አንቀጽ እንደዛ እያልክ በወር ውስጥ ግማሽ ምዕራፍ ትደርሳለህ፡፡ እስከ አመት እንደዛ አድርገህ አንብብ።ይኼን ማድረግ ትችላለህ አይደል?

**እኔ**፡ ቀላል ነው ይኼማ ከዛም በላይ ላነብ እችላለው

**አባታችን**፡ አደራህ ካልኩ በላይ አትጨምር ከሁለት ሳምንት በኋላ ሳታነብ ከቆየህ ግን ወደበኋላ ተመልሰህ አንደ አዲስ አንብብ።ትልቁ ነጥብ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ ግድ ነው፡ ፡ከዛ ያነበብከው ቃላት ኪዳን ወደ ጽሎት መቀየር ነው፡፡ አንብበህ ብቻ ዝም አትበል፡ ፡አምላክ ከፈቀደው እንዴት ብየ መጽሐፍ ቅዱስ አነባለው በሚለው ርዕስ በሰፊው እንወያይበታለን።

> ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ ሆነህ ለመቅረብ ደረጃ በደረጃ ነው፤ቀስ በቀስ መጥፎ ሃሳቦች ሙሉ በሙሉ ይደመሰሳሉ።
> (ቅዱስ መቃርዮስ ዓቢ)

**እኔ**፡ አባቴ ለጓደኛየ ግን በቀን ሦስት ምዕራፍና የጸሎት ሰዓታትን እንድያነብ ፈቅደውለታል፤ታድያ እንዴት ለእኔ አንድ ጥቅስ ብቻ አባቴ??

**አባታችን**፡ ጓደኛህ አሁን አንተ እንደጀመርከው እሱም ይኼን ዘዴ ተጠቅሟል ቀስ እያለ ግን ወደዚህ

ደረጃ ደረሰ::ልክ እንደ ሰውነታችን እድገት በመንፈሳዊ እድገት ላይም በደረጃ መሔድ በጣም አስፈላጊ ነው።

**እኔ፡** መልካም ስለወንጌል ማንበብ ይህ ነው ስለ ጸሎትስ?

**አባታችን፡** ጸሎት ካደረክ ስንት ጌዜ ሆነህ ልጄ?

**እኔ፡** አላስተውስም ለረጅም ጊዜ ነው ከአመት በላይ ሆኖኛል።

**አባታችን፡** እሺ !! አሁን በዚህ ሳምንት አንድ ደቂቃ የሚያክል ጸሎት አድርግ፤ በሁለተኛው ሰምንት ሁለት ደቂቃ፤ በሦስተኛው ሳምንት አምስትደቂቃ ሳታበዛ ሳታሳንስ ጸሎት አዘውትር::

**እኔ፡** ምን ብየ ልጸልይ?

**አባታችን፡** የምትፈልገው ነገር በእንደዚህ መልኩ ጸልይ

(መንፈሳዊ ጉዳይ፡ስጋዊ ጸሎቶች ፡ለሌሎች መጸለይ)።

**እኔ፡** እንዴት ማለት?

**አባታችን፡** ለጌታ ከኃጢአት ከመጥፎ ነገሮች ከፈተና እንድያድንህ ተማህጸነው::‹‹አ አምላኬ ይቺንም ያንንም አድርጌለውና ማረኝ›› ብለህ ምህረት እንደምትቀበል አምነህ ለምነው::ከልብህ በመነጨው ደስታ ስለ ስራህ፣ ስለውሎህ፣ስለፍላጎትህ፣ስለጽናትህ እንዲረዳህ ለምነው::

ለቤተሰብህ (አባትህ፣እናትህ፣ ልጆችህ.....የተጣሉህም ለሚጠልሁም ጸሎት አድርግላቸው)።

**እኔ**፡ ለምጠላቸውም ደሞ ጸሎት ላድርግላቸው!! እንድያዉም ካሳ ክፈሉኝ ልበላቸው አንጂ!

**አባታችን**፡(ፈገግ እያሉ) አይሆንም ልጄ!! ካሉበት ሁኔታዎች እንዲገላገሉ ጸሎት እናድርግላቸው እንጅ ። ጠላትህን ልትቀይረው የምትችል ትክክለኛው መንገድ ጓደኛህ ማድረግ ነው። ከእርሱ ጋር እንድትግባባ የሚያስችል ልቦና ስጠኝ ብለህ ጸሎት አድርግ።

አንተም ጠላትም ከመከራ እንድትገላገሉ ጸሎት አድርግ። የሰው ልጅ ምንም አያውቅም። ሰይጣን ግን እርሰበርሳቸው እንዲጣሉ ይገፋፋቸዋል።ስለዚህ እግዚአብሔር ለአንተና ለጓደኛህ እንዲገላግላቹ ጸሎት ማድረግ ወሳኝ ነው። እስኪ አሁን እየሰማሁ እንደተማርነው አድርገህ ጸሎት አድርግ።

**እኔ**፡ እንዴት አድርጌ ልበል?

**አባታችን**፡ ሁጸጊዜ እንደዚህ ብለህ ጸልይ "በእውነት አምላኬ እኔ ኃጢአተኛ እና ክፉ እያለሁኝ ትወደኛለህን? ምናልባት ሰዎች አያውቁም ይሆናሉ፤አንተ ግን ሁሉንም ኃጢአቴንና የሱሶቼ ኃጢአቶች ታውቃለህ፤ለማቋረጥ ባልወስን አንኳን ትቀበለኛለህ።ለመተው ብዙ ጊዜ ሞክሬ ነበር ግን አልቻልኩም። አ አምላኬ አንተ አባቴ ነህ አይደልን፤ ከዚህ የኃጢአት ሱስ ልርቅ እፈልጋለው፤

ደካማ ስለሆንኩኝ ርዳኝ::አ አምላክ ፍቅርህን ግለጽልኝ፤ ከአባቴንና እናቴን፣ ጓደኞቼ አስበልጠህ እንደምትወደኝ ግለጽልኝ:: አባቴና እናቴን ወደጇ ሁነኝ፣ ብርሃንህን አሳየኝ፤ከአንተ ሳይገባኝ ርቄ የሰይጣን ተገዢ ሆኜ ያሳለፍኩት ጊዜ ይበቃኛል።አሁን ግን ጥሩ አድርጌ አውቄሃለው ስራየን እንጂ እኔን እንደማትጠላ አብልጠህም በጣም እንደምትወደኝም ገብቶኛል። ከአንተ መለየት ውርደት፣ግዛትና ፍራት ነውና ወደ አንተ መልሰኝ::አ አምላኬ ወደ ኃጢአት እንዳልመስ እርዳኝ፤ ብደክምም እንኳን ተስፋ ሳልቆርጥ እኔ ትርጉም የለኝም ከማለቴ በፊት ወዳንተ እንድመለስ እርዳኝ፤ በኃጢአት ተስፋ ቆርጬ ለኃጢአት እጇን እንዳልሰጥ፤ ኃጢአትን ከአንተ ጋር ሆኜ እስከ ሞቴ እንድታገል ተስፋህን ስጠኝ፤ ቃልህ ስለታም ሰይፍ ነውና ለሰይጣን እድታገለው ስጠኝ፤ እማላውቀውንም ነገር አሳውቀኝ፤ ከአሁን በኋላ በሕይወቴ ወስጥ ስልጣን ያለህ አንተ ነህ፤ በምድርና በሰማይ ለዘላለም ከእኔ ጋር እንደምተሆንም እተማመናለው፤ አንተ ወዳጇ የሕይወቴ አባት ነህ።

**አባትችን**፡ እስኪ አሁን በውስጥህ ያለው የሚሰማህ ሁሉም ነገር እስኪ ግለጽለት

**እኔ**፡ አሁን? ስለ እውነት እንዴት አድርጌ እንደምጸልይ አላውቅም::ማለቴ አለመድኩኝም ብልም እንኳን እንደ ባህላዊ ወግ ነው እንጂ የምለው አሁን እንደሚሉት በጣም ከባድ ነው!!!

**አባታችን**፡ ደህና ጀምርና ከዛ ትለምደዋለህ ፡ውስጥህ ላይ ያለው እውነተኛ ሁኔታህ ብቻ ግለጽለት እንጂ ከአሁን በፊት የምታውቀው ጸሎት እና የተለማመድከው ጸሎት አይደለም፡፡ ወድያው መልስ አትጠብቅ።

**እኔ**፡ ታድያ ብሳሳት እንኳ አምላክ ይቆጣኛል?

**አባታችን**(በፈገግታ)፡ አንደኛነገር ቀድመን እንደተናገርነው እግዚአብሔር አምላካችን ውስጥህ ሁኖ እያደከመህ ያለው ኃጢአትህን እንጂ አንተን አይቆጣም፡ ፡ ሁለተኛ እግዚአብሔር የተናገርከውን ቃል እኩል እንደ ቅዱሳን ጽሎት አድርጎ ስለሚቆጥረው ይደሰታል እንጂ አይናደድም።

**እኔ**፡ አባቴ ይቅር በሉኝ እንጂ አነጋገሮት አዲስ ሆኖብኛል!! እኔ ነብሴ ሁሉ በኃጢአት የተሞላሁኝ ሰው ፡ጸሎቴ ልክ እንደ ቅዱሳኖች ይቆጠራል?!!

**አባታችን**፡ አንድ አባት ብዙ ልጆች ነበሩት፡፡ ከነዚያም ልጆቹ እንዱ አፉ ያልፈታ ትንሽየ ልጅ ነበረው፡፡ታዲያ ከሁሉም ልጆቹ ማንን ነው አብልጦ በደስታ ሲያወራ የሚያዳምጠው ትላለህ?

**እኔ**(በፈገግታ)፡ ሁሉንም ጥያቄ በምሳሌ ነው የሚመላሱት. . . እሸነፉኝ፡፡"

**አባታችን**፡ አንድ የስጋ አባት ለልጁ ሊጨክንበትና ሊቆርጥበት ይችላል፤እግዚአብሔር ግን ከማንም አባት በላይ ፍቅር ነው፤የእግዚአብሔር ፍቅር ከእናት ፍቅር

እንኳን በእጥፍ ይበልጣል፡፡ ለዛም ነው መጽሐፍ ቅዱስ አባቴና እናቴን ቢተውን እንኳን አምላኬ ያስጠልለኛል የሚለው። እሱን እንደ አባትህ ወይም እንደ እናትህ አናግረው፤ካልሆነም እንደ ወዳጂህ እድርገው፡፡

**እኔ**፡ በእርግጥ ይኼን ላደርግ እችላለው?

**አባታችን**፡ በእርግጥ ነው የኔ ልጅ፡፡ እደዚህ ይለናል «እናት ልጇን እደምትሸከመው፣ እግዚአብሔር አምላክ ወደዚህ ቦታ እሰክትመጣ፣ በበረሃ በሁሉም በሔድክበት መንገድ እንደሚሸምህ አስብ። እልፍ ብሎም በትንቢተ ኢሳያስም “እናት ልጅዋን እንደምታጽናና፣ እንደዛ ያጽናናቸዋል” (ኢሳ. 66፡13) የሉቃስ ወንጌልም በተራውም “ወዳጆቼ እላቸዋለው አትፍሩ“ (ሉቃ 12፡4) የሚል ተጽፎ እናገኘዋለን።

**እኔ**፡ አባቴ ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው ስሰማው፡፡ የት ተደብቆ ነበር፤ ለምንድነው በልጅነታችን እግዚአብሔርን በራቅንበት ጊዜ፣በብዛት ኃጢያት ላይ በወደቅንበት ጊዜ ለምን አልተሰበከልንም?!!

**አባታችን**፡ እግዚአብሔር ይህ መልካም ስራውና ቃሉ እሱ ለሚመስሉ፣ፍቃዱን ለሚሹ አገልጋይዎቹ ሁሌም ይገልጽላቸዋል ልጄ፡፡ አሁን ግን ያንተ ተራ ነውና ከእግዚአብሔር ጋር አውራ።

እኔ፡ እሺ ካሉማ በቃ ላውራው፡፡ “አቤቱ አምላኬ አኔ ደካማ ስለሆንኩኝ ምን ብየ እንኳን መጸለይ እንዳለብኝ አላውቅም፡ ምንም እንኳን ኃጢአተኛ ብሆንም ወደሽኛል።ከኃጢአቴ የምያታነጻኝና የምታያድነኝ አንተ ነህ፤ደካማ ስለሆንኩኝ አንድ ነገር እንኳን ማድረግ የምችለው ወዳንተ መጥቼ ምህረትህ መለመን ብቻ ነው። ለሁልተኛ ጊዜ ኃጢአት ላይ እንዳልወድቅ እሰጋለው፡፡አባታችን እንዳሉትም ብወድቅም ወዳንተ እመለሳለው ተስፋ አልቆርጥም። አምላኬ እፈልግሃለው፡፡ እንዴት አድርጌ ያለማቃርጥ ጸሎት እንደማደርግ አንተ አስተምረኝ። ከሰይጣን ዝሙት፣ምኞት፣ሱስ የምታድነኝ አንተ ብቻ ነህ፡፡ አሜን!!!

**የባርያህ ስራ ላይ ተሳተፍ (ስርዓተ ቅድሴ)**

አባታችን፡ ሁለተኛዋ ልምምድ ይህች ናት፡፡ ሁልጊዜ ጠዋትና ማታ እንደዚህ እያልክ ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገር፡፡ የሚመጣው ሳምንት ወደ ሌላ ትምህርት እስክንማር ድረስ በንደዚህ ተለማመድ፡፡ የሚቀይርህና ወደ ንሐሃም የምያቀርብህ ጸሎት ነው ።

ቅዱስ ማር ኢስሓቅ

**“ያለጸሎት በሌላው መልክ ወደ ንስሐ የሚውሰደን መንገድ አለ ብሎ የሚያምን ሰው ሰይጣን ያማከረው ብቻ ነው”**። የኼንን ሲለን ትልቅ ትምህርት ነው የተወልን።

**ሦስተኛ ልምምዳችን፡** ሁልጊዜ እግዚአብሔርን እናውራው። መንገድ ላይ፣ትምህርት ቤት፣ስራ ቦታ፣ ታክሲ ውስጥ፣ ውስጥህ ላይ ያለው ያልታየ ነገር ሁሉንም አናግረው፣ ጸልይ። የቅርብ ወዳጅህ ካደግከው በኋላ ሰይጣን አንተን መፍራት ይጀምራል። በተከታታይ ከጌታችን ጋር ተገናኝ። ሁሉም ቅድሳን አባቶቻችን በተከታታይ በእንቅልፍ ሰዓታቸው ሳይቀር ኢየሱስ ክርስቶስ ብለው ስለሚጸልዩ ሰይጣን በጣም ይፈራቸዋል ።

**አኔ፡** ስለእውነት አባቴ ጸሎት ካደረግኩኝ በኋላ ውስጤ ቀለል አለው። ጽሎት እንደዚህ ከሆነ በእግዚአብሔር ብርታት ሁልጊዜ ጸሎት አደርጋለው። በጣም ቀላልና ጣፋጭ አጀማመር ነው። በምችለው አቅሜ ግን በስራም ቦታ ይሁን በመንገድ በማንኛው ሰዓት እጸልያለው። በማንኛውም ሰዓት እማይጸልይ ሰው ምን ያህል የእግዚአብሔር ጸጋ እያለፈው እንደሆነ ይታየኛል።

**አባታችን፡** በል የተማርነውን ማተጠቃለያ እናድርግበት!

**+ አንደኛው ነገር ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአተኞች እንደሚወድ የሚያረጋግጥልን መጽሐፍ ቅዱስ ነው ብለናል፡፡**

**+የእግዚአብሔር ፍቅር ሚስጢሩ ለመረዳት፣ ከሰይጣን ግዛት ለመላቀቅ በሮሜ መልእክት 5፡8 የሚገኘው ጥቅስ ወሳኝ ነው፡፡ “ነገር ግን እኛ ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለእኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለው የእርሱን ፍቅር ያስረዳል”፡፡**

## +ልምምዶች

1. **በመጀመርያ ሳምንት አንድ ጥቅስ በየቀኑ፣ በሁለተኛ ሳምንት ሁለተኛ ጥቅስ በየቀኑ፣በሦስተኛው ሳምንት አንድ አንቀጽ በየቀኑ እንደዛ እያልክ ሒድ በሩብ ዓመት ግማሽ ምዕርፍ ትይዛለህ፡፡**

2. **ጸሎት** በመጀመርያ ሳምንት አንድ ደቂቃ በየቀኑ፣ በሁለተኛ ሳምንት ሁለት ደቂቃ በየቀኑ፣ ለሦስት ወር አምስት ደቂቃ ብቻ ጸሎት አድርግ።ከዚ አታጉድል አታብዛ፡፡ **እግዚአብሔር መንገዱን እንዲያሳይህ እና ጽኑ እምነት እንዲሰጥህ ለምነው!**

3. **ከእግዚአብሔር ጋር ሁልጊዜ አውራ። በስራ ቦታ፣ በመንገድ ላይ፣ ስትተኛ ስትነሳ ሁሌም ወደ እግዚአብሔር ጸልይ።**

በል ደህና ሁን ልጄ! የጌታችን ጸጋ ካንት ጋር ይሁን። በሚመጣው ጊዜ የተረፈው ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢአተኞች እንደሚወድ በማስረጃ እናየዋለን። ይህንን ይተማርነውን በተግባር አውል እናም በየሳምንቱ እየተገናኘን።

አዲስ መንገድ ጀምር (ወይም የሚቀጥለው ርዕስ አንበብ) መጀመር ብቻ በቂ ስላልሆነ መቀጥልና ማጥናት አስፈላጊው ነጥብ ነው።

በፒዲኤፍ (PDF) መልክ ለማግኘት ከፈለጋቹ በሚከተለው አድራሻችል ጻፉልን፡-

Godlovehostel@gmail.com

ወይም በዌብሳይታችን Mbade2.com